የካቲት 9 ቀን 2006 ዓ.ም.
(February 16, 2014)

# “የአሲምባ ፍቅር” መጽሐፍ በካህሳይ አብርሃ ብስራት
## (ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም።)

“የአሲምባ ፍቅር” መጽሐፍ በአቶ ካሕሳይ አብርሃ ብስራት የግል ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን እውነተኛ ታሪክ (autobiography ወይም memoire) ሆኖ ደራሲው አማኑኤል በሚል የድርጅት ህቡእ ስም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ታጋይ ሆኖ ያሳለፈው የትጥቅ ትግል ውጣ ውረድ ዙሪያ ያተኩራል። በዚህም ሁለት ዓበይት ሁነቶችን እናያለን። አንዱ አማኑኤል ድላይ ከምትባል ታግላ ከምታታግል ቆራጥ ታጋይ ጋር የነበረውን የፍቅር ሕይወት የሚዳስስ ሲሆን ሌላው ደግሞ አማኑኤል በሕይወት ቆይቶ እንዲኖርና ይህንን ታሪክ ለመጻፍ ያስቻለውን፣ ከደርግ ታጣቂዎች ጋር በተደረገ ትንቅንቅ አማኑኤልን ማርኮ ነገር ግን መግደል እየቻለ ያልገደለውንና ለጨካኞች አሳልፎ መስጠት እየቻለ ደብቆ ወደ መጣበት የሸኘውን የይመር ንጉሴን ርህራሄ እናያለን። እነዚህ ሁለት ሁነቶች የመጽሐፉ አበይት ማጠንጠኛዎች ናቸው ማለት ይቻላል።

መጽሐፍን ለመጻፍ ሦስት ዓበይት ቅድመ ሁኔታዎችን ማሰብ ይጠይቃል። አንዱ በትምህርት ወይም በሕይወት ተሞክሮ የዳበረ እውቀት ነው። ሁለተኛው የመጻፍ ልዩ ክህሎት ነው። አንዳንዱ በተፈጥሮ የተሰጠውን ልዩ ስጦታ (natural endowment) ተጠቅሞ ይጽፋል። አንዳንዱ ደግሞ በተፈጥሮ የተሰጠውን ልዩ ተሰጦኦ በትምህርት አጎልብቶ በተሻለ ሁኔታ ይጽፋል። ሁሉም ሰው ግን የመጻፍ ተሰጦኦ የለውም። ለዚህም ነው የሚጽፈው ጥቂት አንባቢው ግን ብዙ የሚሆነው። ሦስተኛው ቅድመ ሁኔታ ደግሞ ድፍረት ነው። መጽሐፍን ለመጻፍ ልዩ ድፍረትን ይጠይቃል። ባንድ በኩል መጽሐፍን መጻፍ አድካሚ፣ ብዙ ጊዜ የሚወስድና ብዙ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን ትልቅ ፕሮጀክት አሳካለሁ የሚያስብል ድፍረት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ውጣ ውረድ አልፎ መጽሐፉ ከታተመ በኋላ አንባቢ እጅ ገብቶ ሲነበብ የሚከተለው ትችት የመቀበል ድፍረት ያስፈልጋል። እጅግ ብዙ የመጻፍ ችሎታ እያላቸው ትችትን ፈርተው የማይጽፉ ብዙ ወገኖቻችን እንደሚኖሩ እሙን ነው። የአሲምባ ፍቅር ደራሲ ግን ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንደሚባለው፣ ትችትን ፈርቶ ሳይጽፍ አልቀረም። አቶ ካሕሳይ አብርሃ ብስራት እነዚህን ሦስት ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ ውጣ ውረዱን ችሎ መጽሐፉን ለአንባቢ አብቅቷል። መጽሐፉ ካንዴም ሁለቴ ታትሞ አንባቢ ተቀራምቶታል። በአቶ ካሕሳይ መጽሐፍ የምናየው ሌላው አብይ ክህሎት ደግሞ ድርጊቱ ከተከናወነ አራት ዓሰርት ዓመታት ያህል ሊያስቆጥር እየተቃረበ ነው። ይህን አስታውሶ በመጽሐፍ መልክ ማቅረብ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ችሎታ ነው። በተለይ ደራሲው የተሳተፈባቸውን አንዳንድ የትጥቅ ትግል ውጣ ወረዶችን በጥልቀት አስታውሶ በቅርብ ጊዜ የተከናወነ እንጂ ይህን ያህል ጊዜ የወሰደ በማይመስል መልኩ ማቅረብ በጣም ተደናቂ ያደርገዋል። መጽሐፉ ልብን አንጠልጥሎ ተነባቢ ከመሆን አልፎ በመጽሐፉ ዙርያ የተሰጡ በርካታ የድምጽና የጽሑፍ አስተያየቶችን፣ ትችቶችን እና አቃቂሮችን ስናይ ደግሞ የተዋጣለት መጽሐፍ እንደሆነ እንረዳለን።

አለመታደል ሆኖ በአገራችን ደፍረው የሚጽፉትን ከማበረታት ወይም የራስን መጽሐፍ ጽፎ ለንባብ ከማቅረብ ይልቅ እጅግ ብዙ የሆነው መልካሙን ነገር እርግፍ አድርጎ ትቶ ጥቂት ድክመቶች ካሉ እነዛ ድክመቶች ላይ በማተኮር መተቸት የተለመደ ሆኖ ይታያል። ከመተቸትም አልፎ አንዳንዴ የደራሲያንን ስብእና በሚነካ መልኩ ዘለፋ አዘል ጽሑፍ ሲታይ ደግሞ በጣም ያሳዝናል። ዶ/ር ገላውዴዎስ አርአያ በታሕሳስ 27 ቀን 2006 ዓ.ም. "ይድረስ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ በያላችሁበት፣ ለአዲስ ዓመት አዲስ ርእዮተዓለም" በሚል ርእስ ([http://www.africanidea.org/New%20year_to_Ethiopians.pdf](http://www.africanidea.org/New%20year_to_Ethiopians.pdf)) በጥንታዊቷ ግብጽ በነበረው ታ ሆተፕ የተባለ ፈላስፋን በመጥቀስ ባደረሱን መልእክት አዎንታዊ መንፈስ ከመያዝ ይልቅ አሉታዊ መንፈስ መምረጣችንን ያሳያል። በስነልቦና ጠበብት እንደሚባለውም ተስፋ ሰናቂነት (optimism) ከመምረጥ ይልቅ ጨለምኝነት (pessimism) መምረጣችንን ያሳያል። አንድ ኦፕቲሚስት ግማሽ ብርጭቆ ወተት ቢያይ ብርጭቆው ግማሽ ያህል መሙላቱን ሲያይ፣ ጨለምተኛው ግን ግማሽ ያህል መጉደሉን ነው የሚያየው። (አንዱ The glass is half full ሲል ሌላው ደግሞ The glass is half empty ይላል ማለት ነው።) ለራስ ጤንነትም ቢሆን ተስፋ ሰናቂነት የተሻለ እንደሆነ ለሁሉም ገሃድ ሆኖ የሚታይ እውነታ ነው። በተጨማሪም አስተያየትና ትችት ጸሐፊዎቹ የመጻፍ ችሎታ ያላቸው መሆኑ ከጽሑፋቸው ማየት ይቻላል። ይህንን የመጻፍ ችሎታቸውን በመጠቀም በአብዮቱ ማግስት የነበረውን የትጥቅ ትግልና የራሳቸውን ተሞክሮ አስመልክተው መጽሐፍ በመጻፍ ለአዲሱ ትውልድ ሊጠቅም የሚችል ቅርስ ቢያስቀምጡ ለራሳቸውም ቢሆን የድርሻዬን ተወጣሁ የሚያስብል የመንፈስ እርካታ ይሰጣቸዋል። አለበለዚያ "ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ" ወይም "ወይ አይሰሩ ወይ አያሰሩ" የሚል ትችትን ያስከትላል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በአብዮቱ ወቅት የነበረው በተለይም የተማረው ትውልድ ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት "ያ ትውልድ" በአንድ በኩል ስናየው የሚያስገርም ትውልድ ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የራሱን ምቾት ትቶ ለወገኑ ሞቾት የቆም፣ ከፊውዳል ቤተሰብ ተወልዶም ቢሆን ለጭሰኛው የወገነ፣ ለዓላማው እስከ ሕይወት መስዋዕትነት የተፋለመ፣ ከትግል ጓዶቹ በፊት እኔ ልሰዋ የሚል፣ ሞትን የማይፈራ፣ የነበረውን አስከፊ ስርዓት በእርሱ መስዋዕትነት ተቀይሮ አብዛኛው ሕዝብና ተተኪው ትውልድ ግን በእኩልነት የሚኖርባት ዴሞክራሲያዊትና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት አገር እንድትኖር የሚመኝ በስልጣን ላይ ያለውን ገዢ ፓርቲን ጨምሮ በተለያዩ ድርጅቶች ተሰልፎ የነበረ ትውልድ ነው። ከዛ ትውልድ በሰማዕትነት ያለፈው በአሰርት ሺዎች የሚቆጠር ሲሆን አሁን ከዛ የተረፈውና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ተበትኖ የሚኖር ከዛ ትውልድ የተረፈ በርካታ አለ። በተለይ አንዳንዱ አሁንም ኢሕአፓዊነት እንደ ሃይማኖረት ተሸክሞ፣ በሕይወት የሌለውን ድርጅት ሕይወት እንዳለው በምናቡ እያሰበ ራሱንና በቅርቡ ያሉትን እያሞኘ የሚኖር፣ "ሞኝስ ዘፈኑ አንድ ነው" እንደሚባለው ከአርባ ዓመታት በላይ አንዱን ዘፈን ብቻ ሲዘፍን የኖረ፣ ጥቂት ጫሂዎች ይዞ የሚጓዝ፣ ከ"ያ ትውልድ" ጋር የማይመደብ ግራ የገባው ጥቂት ክፍል ግን አሁንም አለሁ እያለ ለመጮህ ይሞክራል። ኢሕአፓን የሚያወድስ አልባሌ የሆነ ጽሑፍ ከተገኘ እሰየው ብሎ የሚያሞግስ፣ ነገር ግን ኢሕአፓን የሚኮንን ቀርቶ ትንሽ ትችት እንኳ ቢያገኝ ግን አካኪ ዘራፍ የሚሉ ፊታውራሪዎችን ያሰለፈ ትርፍራፊ ትውልድ ነው። እርሱ እየጮኸ ሌሎችንም ሁሉ ጸጥ አስብሎ ቆይቷል። በቅርቡ ነው 'ሳይለንት መጀሪቲ" የሚባለው መተንፈስ የጀመረው። ናፖልዮን ቦናፓርት አለው የሚባል አንድ አባባል አለ- "ዓለማችን ይበልጥ የምትሰቃየው በክፉ ሰዎች ኹከት ሳይሆን በመልካም ሰዎች ጀሮ ዳባ ልበስ ማለት

ነው" የሚል ነው። (The world suffers a lot. Not because of the violence of bad people. But because of the silence of good people.") እነዚህ ወገኖች ከማወክ ወደ ኋላ አይሉም። ይብቃችሁ ማለት ያለበት በርካታ ቁጥር ያለው ነገር ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ያለው ነው። እርሱ በቃችሁ ሊላቸውና አስፈላጊ ከሆነም ኮንፍራንት ሊያደርጋቸው ይገባል።

በአሲምባ ፍቅር ከተሰነዘሩት ትችቶች አንዱ ደራሲው ከታጋይ ድላይ ጋር የነበረው የፍቅር ሕይወት ነው። በተችዎቹ እይታ ታጋይ ድላይ ከአማኑኤል ጋር ምንም አይነት የፍቅር ሕይወት ሊኖራት እንደማይችል ነው የሚገልጹት። ታጋይ ድላይ ታግላ የምታታግል ጀግና እንደነበረች ብዙዎች በትግሉ የተሳተፉት አጋሮችዋና የሚያውቁዋት ብዙ ሰዎች የመጽሐፉን ደራሲ ጨምሮ የሚስማሙበት እውነታ ነው። ነገር ግን ታጋይ ድላይ ከሰው ህልዎና በላይ ያልሆነች ሰብአዊ ፍጡር ስትሆን እንደማንኛውም ሰው የምትደሰት የምታዝን፣ የምትስቅ የምታለቅስ፣ የምትራራ የምትጀግን፣ የምትበረታ የምትደክም፣ የምትተኛ የምትነቃ፣ በመጨረሻም እስከ መጨረሻው የምታንቀላፋ ሰው ነበረች። ስለሆነም ከአማኑኤል ጋር ገደብ ያልዘለለ የፍቅር ሕይወት ማሳለፋቸው ምኑ ላይ ነው ኃጢአቱ? እንዲያውም ታጋይ ድላይ እና አማኑኤል ለድርጅታው ዓላማ ቅድሚያ ሰጥተው፣ በአፍላ ዕድሜያቸው ሊፈትናቸው ለሚችለው የወጣትነት ጾታዊ ግንኙነት ገደብ አበጅተውና እስከመጨረሻው ጸንተው ሲገኙ ሊያስደንቃቸው እንጂ ሊያስኮንናቸው አይችልም። ሁለቱም ታጋዮች ለድርጅታቸው የነበራቸው ፍቅር ከጾታዊ ፍቅር አስበልጠው ተገኝተዋል። ደራሲው ያስቀመጠልን ይኽንን ነው። መጽሐፉን መጻፉ ድላይ የበለጠ እንድትታወቅ አደረጋት እንጂ በምንም መልኩ አንሳ እንድታይ አላደረጋትም። ይህ ደግሞ አበጀህ ያስብላል እንጂ አያስተችም። ደራሲው ለታጋይ ድላይ የነበረው አድናቆት በጽሑፉ እንዳየነው የበለጠ እንደሆነ እንጂ ሌሎች ከሚሉት የሚያንስ አይሆንም። ከዚህ መተጨማሪ ደራሲው ሌሎች ታጋዮችን በመጽሐፉ በማካተት ስማቸው አንደ ገና እንዲጠራ አደረገ እንጂ አላጎደፈም።

ከተሰነዘሩት ትችቶች ሌላው ለምን ስለ ኢሕአፓ ብቻ ተናገርክ? ለምን ስለ ወያኔ አላወራህም? ለምን ወያኔን አልነቀፍክም? የሚል ነው። በዚሁም ምክንያት ደራሲውን የወያኔ እንደራሴ፣ መጽሐፉን ደግሞ በወያኔዎች ተከርክሞ የቀረበ በረከት አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል። ደራሲው መጽሐፉን የጻፈው በራሱ ሕይወት ዙርያ ሆኖ በወቅቱ ሲታገልለት የነበረው የኢሕአፓ ወታደራዊ ክንፍ ስለ ነበረው ስለ ኢሕአሠ ነው። አስፈላጊ ሆኖ በተገኘና መጠቃቀስ ሲያስፈልግ ስለወያኔ ይሁን በወቅቱ ሲንቀሳቀሱ ስለነበሩት ስለ ኤርትራ ሽምቅ ተዋጊዎችም ጠቃቅሷል። ነገር ግን የመጽሐፉ ታሪክ ዳራ ደራሲው በግልጽ እንዳስቀመጠው እርሱ ራሱ ሲታገልለት በነበረው በኢሕአሠ እና በደራሲው ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። ስለ ወያኔና ኢሕአሠ ግንኙነት አስመልክቶ የሚጻፍ ጽሑፍ ራሱ የቻለ መጽሐፍ ይወጣዋልና ሌሎች ታሪኩን በደንብ የሚያውቁት ሊያስቡበትና ይህንን አስመልክተው መጽሐፍ ሊደርሱ ቢችሉ መልካም ነው። ጊዜው እየመሸ ነውና ከተቻለ ሳይጨልም ቢጻፍ ይበጃል። ደራሲው የነበረበትንና የተሳተፈበትን ግን "ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ እንዲሉ" ይኸው መጽሐፉን ጽፎ አቅርቦልናልና አበጀህ ልንለው ይገባል። በዚህ ትችት ላይ ያለው ነጥብ በይበልጥ የሚያተኩረው አሁንም ለምን ወያኔ አልተነካም ከሚል አልፎ ለምን ኢሕአፓ/ኢሕአሠ ተነቀፈ በሚል ምክንያት ነው። ደራሲው የነበረበትን እንጂ ያልነበረበትን አስመልክቶ ቢጽፍ ጽሑፉ መልካም ሊሆን አይችልም። ያም ሆኖ ነቀፌታው ይህን ያህል የሚቆረቁር አልነበረም። ትእዛዝ የሚሰጠው በወቅቱ ፖለቲካ አመራሩን የያዘው ኢሕአፓ ሲሆን በየሸንተረሩ ሲዋጋ የነበረው ግን ወታደራዊ ክንፉ ኢሕአሠ ነው። በሁለቱ መካከል የነበረው የአመራር አሰጣጥ ክፍተት ምክንያት ደራሲው በውቅሮ ጦርነት የበረውን እንደገለጸልን ፖለቲካዊው አመራር ትእዛዝ ብቻ እየሰጠ ነገር ግን ጦርነት ሲካሄድባቸው የነበሩ ቦታዎችን ይበልጥ የሚያውቀው ወታደራዊው ክንፍ ጦርነት ማካሄዱ በደርግ ወታደሮችና እና በኢሕአሠ ታጋዮች የነበረውን የኃይል አሰላለፍ አይቶ ለድል እንደማያበቃ ሲያውቅ ራሱ ወስኖ የመሰረዝ ስልጣን ሊሰጠው ሲገባ በጭፍን ትእዛዝ ታጋዩን እንዲማገድ ማድረግ ካልተተቸ ምን ሊተች

ይችላል? እንደዚህ አይነት ስሕተቶች የኢሕአሠ ታጋዮችን ስሜት የሚነኩ ከመሆንም አልፈው ድርጅቱን ጥለው እንዲሄዱ አስገድደዋቸዋል። ኢሕአፓንም እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ህልውናውን ካሳጡ ምክንያቶች መካከል እንደ ትልቅ ምክንያቶች ሊወሰዱ ይችላሉ።

የአሲምባ ፍቅር መጽሐፍ ከስነ ጽሑፍ አንጻር ሁለት ነገሮች ማለት ይቻላል። በአንዱ በኩል የመጽሐፉ ተነባቢነት ሲሆን ሌላው ደግሞ የደራሲው የቦታዎችና የድርጊቶች አገላለጽ ነው። መጽሐፉን ማንበብ የጀመረ ሰው መጽሐፉን አንብቦ እስከሚጨርስ ድረስ ልክ እንደ ልቦለድ መጽሐፍ ልብን አንጠልጥሎ ቶሎ የሚነበብ መጽሐፍ ነው። በተጨማሪም መጽሐፉ በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ በተለይ ደራሲው የተሳተፈባቸውን ወታደራዊ ፍልሚያዎች እና የተመላለሰባቸውን ተራሮች፣ ሸለቆች፣ ጋራ ሸንተረሮች በጠቅላላ በቦታ ሆኖ የሚያዩት በሚመስል መልኩና የአእምሮ ምስል ሊቀርጽ በሚችል አቀራረብ ያስቀመጠው በመሆኑ ይበል የሚያስብል ነው። የአሲምባ ፍቅር መጽሐፍ የስነጽሑፍ ውጤት ከመሆኑ በተጨማሪ ታሪካዊ ይዘት ያለው በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው። በአብዮቱ ወቅትም ይሁን ማግስት ደርግን ጨምሮ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ታጣቂ ኃይሎች ታሪክ አስመልክተው የተጻፉ የታሪክ መጻሕፍት ይሁኑ የልብወለድ መጻሕፍት እጅግ ጥቂት ናቸው። በተለይ በወቅቱ እድሜያቸው ለትግል ያልደረሰ ይሁን አዲሱ ትውልድ የነበረውን ታሪካዊ ሂደትና እንቅስቃሴ አስመልክቶ የሚጻፉ ጽሑፎችን በእጅጉ ያስፈልጉታል። በአገራችን ታሪክ ለመልካም ተብሎ የተጀመረው ነገር ግን በወታደራዊው ደርግ ተጠልፎ የተወሰደው የሕዝብ ንቅናቄ አስመልክቶ ብዙ መጻፍ ይኖርበታል። አቶ ካሕሳይ አብርሃ ብስራት ያደረገው ይህንን ነው። በራሱ ህይወት ዙርያ ያጠነጠነ የግል ታሪክ ቢሆንም በወቅቱ በተለይ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ወታደራዊ ክንፍ የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ታሪክ አስመልክቶ ያቀረበው በመሆኑ እጅግ አስፈላጊ የታሪክ መጽሐፍ ያደርገዋል። ሌሎች በወቅቱ በፖለቲካዊ አመራር ይሁን በወታራዊ ክንፉ ወገን ሆነው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ታጋዮች አቶ ካሕሳይ እንዳደረገው ቢዘገይም የድርሻቸውን ቢያበረክቱ ለራሳው የመንፈስ እርካታ፣ ለአዲሱና ለመጪው ትውልድ ደግሞ ትልቅ ማስተማሪያ የሚሆን አበርክቶ ነው። ቢዘገይም መጻፍ ያለበት አሁን ነው። በጣም ዘገየ የሚባለው ከአሁን በህዋላ በዕድሜም እየገፋ፣ አቅምም እያጠረ፣ የማስታወስ ችሎታም እየቀነሰ ሲሄድ ነው። እንግዲህ ልብ ያለው ልብ ይበል።

በመጨረሻ ደራሲው አቶ ካሕሳይ አብርሃ በበረሃ ታጋይ ሆኖ የነበረውን ጽናት በትምህርት ላይም በድጋሚ አስመስክሯል። ብዙ ውጣ ውረድ አልፎ በሱዳን በኩል ወደ ፖርቶሪኮ ከዛም ወደ አሜሪካ በትምህርት ምክንያት ከመጣ በኋላ መኖርያውን በኮሎራዶ ስቴት በዴንቨር ከተማ አድርጓል። በዚህ ቆይታውም ድሮ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ትግል ሲቀላቀል የተማሩት ባልተማሩት ላይ የነበራቸውን አመለካከት ባሳደረበት ቁጭት፣ እንዲሁም በትግሉ ምክንያት በተቋረጠበት ነገር ግን በውስጡ በነበረበት የትምህርት ጥማት ለማርካት በዩኒቨርሲቲ ኦቭ ኮሎራዶ በመግባት የፋርማሲ ትምህርት ተከታትሏል። በዚሁ የሥራ መስክም ተሰማርቶ ከቤተሰቡ ጋር ኑሮውን ይመራል። ኮሎራዶ ስቴት ውስጥ ከሚገኙት የቱሪስት መስህቦች መካከል አንዱና ዋነኛው ሮኪ ማውንትን ናሽናል ፓርክ ነው። ካሕሳይ ሮኪ ማውንትንስን ሲያይ ልክ የወጣትነት እድሜውን ያሳለፈባቸው ተራሮች ስለሚመስሉት በጣም እንደሚወዳቸውና መኖሪያውም በዚሁ አካባቢ እንዲያደርግ ምክንያት እንደሆኑትም ይገልጻል። ለአሲምባ የነበረው ፍቅርና በውስጡም ያሳለፈው የፍቅርና የትግል ሕይወት ምክንያት በማድረግም መጽሐፉን “የአሲምባ ፍቅር” በማለት ሰይሞታል። አቶ ካሕሳይ/አማኑኤል በሕይወት ዘመኑ ሊያደርጋቸው ከሚገቡ መልካም ነገሮች መካከል ይህንን መጽሐፍ ጽፎ ለንባብ ያበቃ በመሆኑ በጣም ሊመሰገን ይገባዋል። Thank you so much Kahsay!

በዶ/ር ወልዱ ሚካኤል ወልደየሱስ
(ወልዱሻ ዘቦልደር)
weldusha19@yahoo.com